# በቤኒሻንጉል ጉምዝ ዛሬም አማራዎችን ማረድ እንዳልቆመ የአዲሱ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ መሪ አስታወቀ

June 22, 2018




(ዘ-ሐበሻ) ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ማንዱራ ወረዳ "ወ/ሮ ይሻሙሽ ፈንታ የተባለች የሁለት ወር ሕፃን ልጅ ያላት እመጫት በገጀራ ጭንቅላቷን ቆራርጠው ፤ አሸብር አለማየሁ እርሻ ላይ እንዳለ በቀስት ህይወታቸዉ አልፏል። በቀስት ሲመታ ፖሊሶች በአካባቢው ነበሩ። ሌሎች ሁለት አማሮች ደግሞ በቀስት ተመተዉ ፓዊ ሆስፒታል ገብተዋል። ትላንት ከፓዊ ወደ ባ/ዳር ሪፈር ተደርጎ የነበር አማራም ፈለገ ህይወት ሆስፒታል እንደደረሰ ህይወቱ ማለፉ ተገልጾልናል፡፡" ሲል የአዲሱ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ መሪ ዶ/ር ደሳለኝ ጫኔ ገለጸ::

"ማንዱራ ወረዳ ያለ ወጣት አማራ ችግሩ የተከሰተበት ቀበሌ ድረስ ሂዶ የተገደሉትን ሰዎች አረጋግጦ ፤ በገጀራ የተገደሉትን ወገኖች ፎቶ አንስቶ ለመላክ ቢሞክርም ሳይሳካለት ቀርቷል፡፡ መገደላቸዉን በአይኑ እንዳየ ግን በስልክ አረጋግጦልኛል፡፡" ያለው ዶ/ር ደሳለኝ " ብአዴን በቤንሻንጉል ጉምዝና በኦሮምያ ክልል ለወራት በዘለቀዉ የአማሮች ግድያና መፈናቀል ተጠያቂ ነዉ፡፡ የአማራን ሞት ለማስቆም የፓለቲካ ቁርጠኝነትና የአቅም ዉሱንነት ችግር አለበት፡፡ አማራን መጠበቅ ያልቻሉ የብአዴን የጸጽታ ባለስልጣናት በአስቸኳይ ስልጣን መልቀቅ አለባቸዉ፡፡ በቸልተኝነት

የአማራን ህይወት እንዲጠፋ በማድረግም ሊጠየቁ ይገባል" ብሏል::

"አይደለም ክልል ቀበሌ መምራት የማይችሉት የቤ.ጉ ክልል ባለስልጣኖችም አማራን የሚገድሉ ጉምዞችን ማስቆም ስላልቻሉ ባስቸኳይ ስልጣን ይልቀቁ" ሲል የጠየቀው ዶ/ር ደሳለኝ "በአንድ ወቅት ቤ.ጉ የሚገኙ ኦሮሞዎችን ለመጠበቅ የኦሮምያ ክልል መንግስት ልዩ ኃይል እንዳሰማራዉ ሁሉ የአማራ ክልል መንግስት የአማራ ልዩ ኃይል አሰማርቶ ወገኖቻችን መጠበቅ መቻል አለበት፡፡" በማለት "የአማራ ግድያና መፈናቀል አሁኑኑ ይቁም ፤ ወንጀለኞች በአስቸኳይ ለፍርድ ይቅረቡ" ሲል ጠይቋል::